# በእውነተኛና ሃይማኖት ባለው፣ በቆራጥ ሕዝብ ዘንድ፣ መልካሙ ኹሉ ይቻላል !

“ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" (የተደበቁ የኢትዮጵያ ምስጢሮች) ከሚለው የንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ሦስተኛ መጽሐፍ የተወሰደ።

ከታላቅ አክብሮትና ምስጋና ጋር።

ዛሬ ባሉትም ሰዎች ዘንድ፣ እንደጥንቱ እየተፈጸመ ከመቀጠል በቀር፣ ሌላ ዕድል ሊኖረው አይችልም ! ምክኒያቱም እውነታ፣ እርግጥ በበለጠ እየጨመረና እየተጠናከረ የኼደ መኾኑን፣ ይኸው፣ እየረሳችን ምስክር በመኾን፣ በገሃድና በግዘፍ እናየዋለን፣ ይኹን እንጂ፣ እየራሳችን ምስክር በመኾን፣ በገሃድና በግዘፍ እናየዋለን፣ ይኹን እንጂ፣ ከሰነፎችና በሰነፎች የሚቀርበው፣ እንዲህ ያለው ምክንያት፣ እዚያው፣ ለሰነፎች የሚያገለግል፣ የሰነፎች፣ ከንቱና ፍሬቢስ አሳብ ሰለሆነ፣ በእኛ፣ በቀዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ፣ ፈጽሞ ቦታ የለውም።

በሓሰተኞችና በእምነተቢሶች ዘንድ፣ ክፉው ኹሉ እንደሚቻል፣ እንዲሁ፣ በእውነተኛና ሃይማኖት ባለው፣ በቆራጥ ሕዝብ ዘንድ፣ መልካሙ ኹሉ ይቻላል ! አንድ ቆራጥ ሕዝብ ከፈለገ ኹሉን ማድረግ የሚቻለው መኾኑን ለማመልከት ባመኑበት እምነታቸውና በፈለጉት ሥርዓታቸው ማንነታቸውን አኩርተው፥ መሪዎቻቸውንም አቅፈው፣ የኃያላን ተቃዋሚዎቻቸውን ጥቃት ተቋቁመው፥ በውጭ ተፅዕኖም ሳይበገሩ፣ ይህን እውነታ፣ በግብር ያረጋገጡ ሕዝቦችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

ከእነዚህም መካከል የዛሬውን ትውልዷን አያድርግባትና ከቀደሙት ታማኞቹ ኢትዮጵያውያን ልጆቿ፣ ምግባርና ገድል የተነሣ፣ ቀንደኛ ኾና በመልካም ምሳሌነት የምትጠቀሰው፣ ኢትዮጵያ መኾኗ፣ በባለጋራዎቿ ዘንድ ሳይቀር የተመሰከረ እውነታ ነው። ለዚህ ቆራጥነት ስለሚያበቃው፣ ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር፣ በዓለም ላይ የሚኖሩት ሕዝቦች፣ የተለያየ ግምት፣ እንዳላቸው፣ ከዚህ የሚከተለው፣ የጊዜያችን ኹነት በቀላሉ ሊያስረዳ ይችላል፦

ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ ኢራቅ ኩዌይትን በወረረች ጊዜ፣ አሜሪካውያንና ምዕራባውያን አገሮች፣ በነዳጅ በኩል ያላቸውን ጥቅም ለመጠበቅ ሲሉ የቃል ኪዳን ጦር አደራጅተው ኩዌይትን በመርዳት ጎረቤቲቱን ሳዑዲ ዓረቢያን ጭምር፣ ከወረራው ማትረፋቸው ይታወሳል። ይህን በመሰለው እርዳታቸው፣ ሊዋጉላቸው፣ ወደእነዚሁ የእስልምና አገሮች የኼዱትን፣ አሜሪካንና የጦር ጓደኞቿን፣ ሳዑዲ ዓረቢያ፣ በቅድሚያ ካስገባቻቸው ግዴታዎች መካከል አንደኛውን ልጥቀስላችሁ ! እርሱም ለእርዳታ የደረሱላት ክርስቲያኖቹ ምዕራባውያን የጦር ጓደኞቿ፣ በሳዑዲ ዓረቢያ ምድር ላይ፣ ሃይማኖታውያን የኾኑ፣ የጸሎትም ኾነ የሰንደቅ ዓላማ፥ ወይም የበዓል ሥርዓቶቻቸውን፣ በምንም መንገድ እንዳይፈጽሙ የሚከለክለው ነበር።

ይህም ማለት፣ "እናንተ ክርስቲያኖች፣ የክርስትና ሥርዓታችሁን፣ በእስልምና ምድራችን ላይ ከምትፈጽሙ ይልቅ፣ እስላሙ ጠላታችን ኢራቅ ወርራን፣ አገራችንን ብትይዝ ይሻለናል !” በማለት፣ ቅድሚያውን ለሃይማኖታቸው መስጠታቸው ነው። በተቃራኒው ደግሞ አሜሪካና ምዕራባውያን ተባባሪዎቿ፣ "እናንተን ሳንረዳ፣ ሃይማኖታችንን ከምናስከብር ይልቅ፣ ለገንዘብ ጥቅማችን ስንል ሃይማኖታችን ቀርቶ እናንተን ብንረዳ ይሻለናል !”ማለታቸው ነው።

ምሥራቃውያንና ምዕራባውያን፣ ስለሃይማኖት ያላቸው አስተሳሰብና ግምት እንግዴህ በዚህ ተለይቶ ይታወቃል። ኢትዮጵያ፣ ከእግዚአብሔር ያገኘችው፥ ጥንታዊ፥ ቀዳሚና የራስዋ የኾነ ሕዝባዊ የአስተዳደር አቋም የሌላት ይመስል፥ እነርሱም ዛሬ እየሠሩበት ያለው ከዚሁ ከእርሷ የወረሱት መኾኑን ለማዘናጋት በመሞከር በአሜሪካና በቀሩት ምዕራባውያን አገሮች ግፊት፣ "በኢትዮጵያ የሕዝባዊ አገዛዝ ሥርዓት (democracy/ዲሞክራሲ) መስፈን አለበት !” ተብሎ ለዚህ ትውልድ ይህን ያህል ነጋሪት የሚደለቅለት ለምን እንደኾነ በቀላሉ መመልከት ነው።

የሳዑዲ ዓረቢያ ሕዝብ፣ ከአሜሪካውያንና በጠቅላላ ከምዕራባውያን ጋር ያለው ግንኙነት ያው በገንዘብ ላይ የተመሠረተ ኾኖ፣ የቱን ያህል የጸናና የተንሰራፋ እንደኾነ በይፋ ይታወቃል። ይኹን እንጂ ግንኙነቱ እንዲህ እጅግ የተቀራረበና የተጠናከረ እንደመኾኑ፥ አገሩም በፈረንጆቹ የሥልጣኔ ምርት እንደመጥለቅለቁ መጠን ሕዝቡ

በሃይማኖቱ ላይ የተመሠረተውን ሥነ ምግባሩን ቋንቋውንና ፊደሉን፥ አለባበሱንና ሌላውን ባህሉን በይበልጥ አጠናከረ እንጂ በምንም መንገድ አልለወጠም።

እንዲያውም ዐረቦች፡ የዘመኑን ትውልዳቸውን በእስላማዊው ሃይማኖታቸው ሥርዓተ ትምህርት እያነፁ በማሳደግ እያዘጋጁት ያሉት በክርስቲያኖቹ ምዕራባውያን ላይ በጠላትነት እንዲነሣ መኾኑ በይፋ የሚታወቅ ከመኾኑ ጋር፡ በአሁኑ ጊዜ፡ ከምዕራቡ የክርስቲያን አህጉር ላይ በእስልምና አክራሪዎች ታውጆ እየተካኼደ ያለው ዓለም አቀፍ የ"ሽብር" ጦርነት በቂ ማስረጃ ነው።

ኢትዮጵያም እኮ እስከዚህ እስከዛሬው ትውልድ ድረስ እንደዚህ ነበረች። ያውም በኧሺሆች ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን። ዛሬ ግን ይህ ትውልድ ከላይ የተጠቀሱትን የአባቶቹንና የእናቶቹን ምሳሌያዊ ምክር ባለማጤንና ባለማስተዋል ወይም ቸል በማለት ወይም በመናቅ እንኳንስ ዓበይት የኾኑትን የተከበሩ ውርሶቹን ሊንከባከብ ይቅርና፡ ጥቃቅንና ተራ የኾኑትን እንኳ መጠበቅ አቅቶት ይኸው፡ ጨርሶ ለመውደቅ፡ ሲፍገመገም ይታያል።

የኢትዮጵያውያን አንዱ የጨዋነታቸው መገለጫ የኾነው የመከባበር ባህላችን በዚህ ትውልድ እየተዳከመ በመኼድ ላይ ይገኛል፤ ለምሳሌ አንድ ኢትዮጵያዊ ቀደም አድርጎ የማያውቀውንና በዕድሜው ከእርሱ ላቅ ያለ መስሎ የሚታየውን ማንንም ሰው፥ ወንድ ኾነ ሴት፡ "እርስዎ" በማለት ወደ "አንቱታ" ደረጃ ከፍ ያደርገዋል፥ ወይም ያደርጋታል እንጂ፡ እንዲያው ተነሥቶ ወንዱን "አንተ!" ወይም ሴቷን፡ "አንቺ!" አይልም ነበር። ዛሬስ፡ ይህ ባህል፡ በምን ኹኔታ ላይ ይገኛል ይህስ የመከባበሩ ባህላችን እየቀረ መኼዱን አያመለክትምን?

የሥጋ ወላጆችን፥ ወንድሞችንና እኅቶችን ብቻ ሳይኾን፡ አዛውንቶችን ወንዶች፡ "አባባ" ወይም ታላላቆችን፡ "ጋሼ" ፥ አዛውንቶችን ሴቶች ደግሞ "እማማ" ወይም ታላላቆችን "እትዬ" ብሎ የመጥራቱ መልካም ባህላችን ደብዘው ሳይቀር፡ እየጠፋ መኼዱን ይኸው እየተመለከትን ነው። እንዲያውም በዚህ ፋንታ በባዕዳን ቋንቋ፡ Father! Mother! Brother! Sister! እያሉ መጥራት በኅብረተሰቡ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነትን አግኝቶ ተጠሪዎቹም፡ በደስታ፡ ወንዶቹ "ወይ!" ወይም "አቤት!"፥ ሴቶቹ፡ "ወይ!" ወይም "እመት!" እያሉ ፈጥነው መልስ በመስጠት ተባባሪነታቸውን ሲያረጋግጡ ይታያል። በነገራችን ላይ "አቤት!" የሚለው ምላሽ የሚሰጠው፡ ጠሪው ወንድ ሲኾን ብቻ እንጂ ለሴት ጠሪ ፈጽሞ "አቤት!" አይባልም፤ ነውር ነው። ለሴት ጠሪ፡ ተጠሪው ምላሹን መስጠት ያለበት "እመት!" ብሎ ነው።

ለዚህም፡ ለኹለተኛው ቁም ነገር፥ በቂ ምክንያት አለ፤ ይኸውም "አቤት!" "አብ የት?" ማለት ሲኾን፡ በግእዝ፡ "አቡየ" አባቴ፥ "አይቴ" የት ማለት ስለኾነ፡ "አባቴ! የጠራኸኝ፡ ወደየት (ወዴት) ልትልከኝ ነው?" ፥ እንደዚሁ ኹሉ "እመት!" "እም የት? ማለት ሲኾን በግእዝ "እምየ" እናቴ፥ "አይቴ"፡ የት ማለት ስለኾነ "እናቴ! የጠራሽኝ፡ ወደየት (ወዴት) ልትልኪኝ ነው?" ማለት ነው ተብሎ ይተረጎማል።

የአለባበሳችን ባህል ስለሚገኝበት ሁኔታ ስንነጋገር በጣም የሚያሳዝነን ነገር ይኖራል። ይኸውም ይህ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ በአለባበሱ ረገድ የራሱን ባህል ጨርሶ ትቶ፡ ፈጽሞ አውሮጳዊ፥ ወይም ምዕራባዊ ወይም ፈረንጅ በመኾኑ ነው።

ዘመናዊውን ትምህርት ከተማረው፥ ከጥራዝ ነጠቁና ከከተሜው መካከል በአኹኑ ጊዜ የአገራችንን ልብስ ለዓውደ ዓመት እንኳ የሚለብሰው ስንቱ ነው? እጅግ ጥቂቶች ናቸ፤ ምናልባት የመልበስ ፍላጎት ኖሮአቸው የሚለብሱ ቢኖሩ እንኳ እነርሱ አለባበሱን ስለማያውቁበት አንድ ባዕድ የኾነ ሰው፡ "እንዲህ አድርገህ ልበሰው!" እየተባለ እንደሚናገረው ተዋናይ መስለው እንደሚለብሱት የሚታወቅ ነው።

በአሁኑ ጊዜ ከጥንታውያኑ የዓለም አህጉር መካከል በዘመኑ ትውልዷ ምክንያት በአጠቃላይ ኹለንተናዋ "ባለቤቱ፡ በቤቱ ባይተዋር፡ ባይተዋሩ በሰው ቤት ባለቤት" የኾነባት አገር ቢኖር ኢትዮጵያ ኾና ትገኛለች። ይህ ዝቅጠት አያሳዝንምን? አያሳፍርምንስ?

የዘመኑን ዓለማዊ ሥልጣኔ እንደሃይማኖት በተከተለው ወገን ዘንድ ከአገር ልብሱ ብቻ ሳይኾን ከለባሹም ሰው ይልቅ የክብሩን ቦታ የያዘው የባዕዳኑ ልብስ ስለኾነ የኢትዮጵያዊነት አንዱ ምልክት የኾነውን "ነጠላ" ወይም "ኩታ" ደርቦ መታየት ለዚያ ሰው በዘመናዊ ትውልድ ዘንድ የመጨረሻውን የውርደትና የንቀት ምልክት ተጎናጽፎ እንደመታየት የሚያስቆጥር ከመኾን ደረጃ ተደርሷል። ይህን እውነታም፡ "ባለኩታ"፥ ወይም "ኩታ ለባሽ" የኾነው

ኢትዮጵያዊ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ በራሱ አገር፥ በራሱ ወገኖች ሳይቀር ሲናቅና ሲዋረድ አይቷል። አዎ! በነገራችን ላይ “በራሱ አገር በራሱ ወገኖች”አያስብልም ምክኒያቱም በባዕዳኑ ዘንድማ እየተደነቀና እየተከበረ ነው ያለው። የተናቀውና የተዋረደው እኮ በራሱ አገር፥ በራሱ ወገኖች ዘንድ ብቻ ነው።

ይህ ኹኔታ የደረሰው በኩታውና በባለኩታው አገር በኢትዮጵያ ከዚያም ይባስ፣ በአገሩ በኢትዮጵያ ስም በሚጠራው አየር መንገድ ነው። ባለኩታው ኢትዮጵያዊ ወደባሕር ማዶ የሚበርበትን የጉዞ ወረቀቱን (Ticket)ለማስቆረጥ፣ በመናገሻዩቱ ከተማ ውስጥ ካሉት የአየር መንገድ ጽሕፈት ቤቶች መካከል በአንዱ እንደተገኘ በተራው የተቀበለችው ጸሓፊ ባለጉዳዩ ባልጠበቀው መልክ አነጋገራና የጉዞ ወረቀቱን አዘጋጅታ እስከሰጠችው ጊዜ ድረስ ለአንድም አፍታ ቀና ብላ ዓይን ለዓይን ሳታየው ከእርሱ ለቀረበላት የምስጋና ሰላምታም እንኳ አጸፋውን በአግባቡ ሳትመልስለት አሰናበተችው።

ያ ኢትዮጵያዊም› “ይህ የኾነው፣ ለምን ይኾን?” እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ከቆየ በኋላ ጉዞውን ለመጀመር በሚሣፈርበት ዕለት በአየር ማረፊያው ተገኝቶ ሣለ በዚያ ከነበሩት የአየር መንገዱ ኀላፊዎች መካከል አንዳንዶቹ፣ ይህን መንገደኛ ለይተው አውቀውት ኖሮ ተመካክረው ከሚበርርበት ከዝቅተኛው የቁጠባ ክፍል ወደከፍተኛው ባለማዕረግ ክፍል ተዛውሮ እንዲጓዝ ወሰኑ ውሳኔውንም በሚነግሩት ጊዜ ያ በማንነቱ ብቻ በልዩ አክብሮት ይታሰብና ይገመት የነበረው ኢትዮጵያዊው መንገደኛ በሰውነቱ ላይ ያን ኩታውን ደርቦ በታያቸው ጊዜ አስተሳሰባቸውና ግምታቸው በቅጽበት ተለውጦ በዚያ አለባበሱ በዚያ የማዕረግ ክፍል መገኘት አግባብና ተስማሚ መስሎ ስላልታያቸው ያን ለእነርሱ “የውርደት ማቅ”፥ ለእርሱ ግን “የክብር ልብሱ” የኾነውን ኩታውን ማውለቅ እንዳለበት እንዲነገረው ተደረገ።

እርሱ ግን ያን አሳብ ባለመቀበል፣ “ኢትዮጵያዊነት”፣ ወይም “ኢትዮጵያዊ ኾኖ መታየት”፣ በትውልዱ ዘንድ ከምን ዓይነቱ የግምት አዝቀት ውስጥ ተወርውሮና ተጥሎ እንደሚገኝ ባየበት በዚህ ገጠመኝ እየተደነቀና እየተከዘ እያዘነም ያንኑ የኢትዮጵያዊነቱን የክብር ምልክት እንደተጎናጸፈ፣ የ”ኢትዮጵያን ስምና “የአንበሳ” ምልክቷን በተሸከመው ጥያራ (Airplane)የበረራ ጉዞውን መቀጠልን መረጠ።

የተመደበለትን የበረራ ወንበር ይዞ በሚጓዝበት ጊዜም ከአስተናጋጆቹ ይቀርብለት የነበረው የውስጥ መስተንግዶ ከውጭዎቹ የተለየ አልነበረም፣ ገና ከመነሻው ጋዜጣና መጽሔት እንኳ ለመንገደኞች በትሕትና ሊቀርብላቸው “ለእርሱ ይኼ ምኑ ነው? አያስፈልገውም!” ተብሎ ይኾን? እንጃ ለእርሱ ብቻ ተነፍጎት ታለፈ!

ወጣቱ ትውልድ የራሱ በኾነው የተከበረ ባህል ላይ ይህን የመሰለውን ድርጊት ከፈጸመ እውነትም ከእንዴት ዓይነቱ የአስተሳሰብ ውርደት ሥር ወድቋል ማለት ነው!?

ይህን የመሰለው ኹኔታ የሚታየው የዕድሜ ወጣቶች በበዙበት አየር መንገዱን በመሰሉ፣ ዘመናውያን ድርጅቶች ዘንድ ብቻ ሳይኾን በዕድሜ ላቅ ያሉ አዛውንት ባሉባቸው አካባቢዎችም ጭምር በባሰ ይዘታ የሚፈጸም መኾኑን ለመጠቆም ይኸው “ጨርቅ ለባሽ” ኢትዮጵያዊ በሌላ አጋጣሚ የደረሰበትን አሳዛኙን ተመሳሳይ ድርጊት እንዲህ ሲል ባጭር ያወጋል።

ነገሩ የሆነው የባለቤቱ የኩታውና የባለኩታው አገር በሆነችው በዚችው በኢትዮጵያ ያውም በዋና ከተማዩቱ በአዲስ አበባ ነው፣ የሚርመሰመሱትም የኩታውና የባለኩታው ወገኖች ኢትዮጵያውያን ናቸው፣ ቦታው ወደውጭ አገር ለሚጓዙ መንገደኞች የኬላ ደብተር (Passport)እና የይለፍ ፈቃድ የሚሰጥበት የቤተ ምልክናው መሥሪያ ቤት ሲሆን ባለጉዳዩ በዝቶ ይታያል። እዚያ ከወንዱም ከሴቱም መካከል ያገሩን ሸማ ተጎናጽፎ የተገኘው፣ አንድ እርሱ “ባለኩታው ብቻ ነው። ከባለጉዳዩም ከሠራተኛውም፣ ሁሉም እርስ በእርሱ “ባለኩታው ብቻ ነው። ከባለጉዳዩም ከሠራተኛውም ሁሉም እርስ በእርሱ ሲተያይና ሲነጋገር እርሱን ግን ማነጋገር ቀርቶ አንድም ሰው ቀና ወይም ዘወር ብሎ የሚያየው የለም።

ጥቂት እንደቆየ ይኸው ባለኩታ እጥላ ሥር ቆሞ የተራ ጥሪውን በሚጠባበቅበት ጊዜ ከባለጉዳዮቹ መካከል እርሱን በጣም የሚያውቀው እንዲያውም በደርግ እሥር ቤት ከሰባት ዓመታት ለሆነ ዘመን አብሮት የነበረ የመከራ ጓደኛው ወደእርሱ አቅንቶ ሲመጣ አየው፣ ደስ ብሎት ሰላምታ ሊሰጠው ዓይን ዓይኑን እየተመለከተ ሲጠባበቀው ሣለ፣ ከፊቱ ሲደርስ ሌሎቹን ሁል አንድ በአንድ እያማተረ አይቶ እርሱን ሳያየው እጥፍ ብሎ ይራመድ ጀመር።

ያ የመከራ ጓደኛው ወዲያ ወዲህ ይል የነበረው በእርሱ በባለኩታው አጠገብና ፊት ለፊት ሰለነበረ፥ “ይህን ያህል ሲመላለስ በአጋጣሚ እንኳ እንዴት ወደእኔ ቀና ብሎ አይመለከትም ! እንዴት ላያየኝና ዝም ሊለኝ ይችላል ! አይቶ እንዳላየ መሆኑ ይሆን? በከባድ አሳብ በመዋጡ ይሆን? አልፎ አልፎ ደግሞ ሌሎችን ያነጋግራል፤ በእኔ የተቀየመበት ነገር ይኖረው ይሆን? ወይስ ከእግር እስከራሱ በምዕራባውያን የከበረ ልብስ ተከውኖና ተሸቀርቅሮ ስለነበረ እኔን፥ “ጨርቅ ለባሽ፥ ገጠሬ ነው” ብሎ መናቁ ይሆን” አይ ! ነጠላ መልበስ ወይም ባላገርነት እንዴት ሊያስንቅ ይችላል?” ለማንኛውም እስኪ ላስጨርሰው ! በማለት ሲያወጣ ሲያወርድ፥ ምናልባት ከእኩል ሰዓት በላይ የሆነ ጊዜን አሳለፈ፤ በመጨረሻ፥ “ሳንነጋገር ቢሄድ ይቆጨኛል ! በእርሱ በኩል ጎደለ በዬ የእኔን ግዴታ መተው የለብኝም ! ”ብሎ፥ ይህ ጉደኛ ጨርቅ ለባሽ ኢትዮጵያዊ ያ ወዳጁና የእሥር ጓደኛው ከአጠገቡ ሲደርስ “አቶ እከሌ ! ” ብሎ ሲጠራው ቀና ብሎ አይቶ “ውይ ! አንተ ነህ እንዴ ! አላየሁህም ነበርኮ ! ” ብሎት ሰላምታ ተለዋውጠውና ተጨዋውተው ተለያዩ።

## <u>የአንድ ቆራጥ ኢትዮጵያዊ የጀግንነት ታሪክ</u>

የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በተለይ ፋሺስት ጣልያን ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ ለፈረንጆቹ አለባበስ፥ አክብሮትን ቅድሚያንና ብልጫን ሲሰጥ ኢትዮጵያዊውን የአለባበስ ሥርዓት ግን በራሱ ሕዝብ ዘንድና በራሱ አገር ሳይቀር ምን ያህል ለውርደት ለጥቃትና ለንቀት እንዳደረገው የሚያሳያውን እውነተኛ ተውኔት እንመልከት፦

በዚህ ነገር እጅግ የሚቆጭ አንድ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ በአንድ ብሔራዊ በዓል ምክንያት በተዘጋጀ የቤተ መንግሥት ታላቅ ግብር ላይ እንዲገኝ፥ የግብዣው ወረቀት ስለደረሰው ጸዓዳ የኾነ የአገሩን ልብስ ለብሶ ልክ በሰዓቷ ሲደርስ በቤተ መንግሥቱ ግቢ የውጭ ደጃፍ ላይ ቆመው በተጨናነቀው ደጀጠኚ መካከል ተጋባዡን የሚያስተናግዱት አጋፋሪዎች እንኳንስ በአክብሮትና በትሕትና ተቀብለው ወደውስጥ ሊመሩት ይቅርና ዘወር ብሎ የሚያየውና የሚያሳልፈው ሰው እንኳ አጣ ! በእጁ እየጠቀሰና እየጮኸ ቢጣራም፥ የሚያዳምጠውና ቁም ነገር የሚሰጠው አላገኘም።

“መቼም እዚህ ድረስ መጥቼ አልመለሰም ! ” ብሎ፥ እንደምንም ተጋፍቶ ከአጋፋሪዎቹ ዘንድ ድረስና ለመግባት ዘው ሲል፥ አንዱ አጋፋሪ በድፍረቱ ተገርሞና ተናዶ “እንዴት አንተ ! ” ብሎ ወደኋላው በኃይል ገፈተረው ! መገፍተር ብቻ ሳይኾን በያዘውም ሽመል ዠለጠው። ኢትዮጵያዊውም ተጋባዥ በዚህ እጅግ ቢያዝንም ተስፋ ሳይቆርጥ፥ “እኔ እከሌ ነኝ እኮ ! ወይም ለእልፍኝ አስከልካዩ ነገሩልኝ ! ” ብሎ የበደለውን አጋፋሪ በጽሙና ቢማጸነውም፥ “ኧ ! ምን? ደሞ፥ 'እኔ እከሌ ነኝ' ይለኛል ! ? የማን ቀልደኛ ነህ? ሂድ ወዲያ ! ” ብሎ እንደገና ሊያጉላላው ሲሞክር፥ ሽሽት ብሎ ቆም ይመለከት ጀመር።

በዚህ መካከል ጓደኞቹ ባለሥልጣኖች በፈረንጆች አለባበስ ተከውነው ሲመጡ ገና ከሩቁ አጋፋሪዎቹ ተጣድፈው ኼደው እጅ ነሥተው ተቀብለው መንገዱን እየከፈቱላቸው ከፊትና ከኋላም አጅበው በክብር ሲያስገቧቸው ይኸው “ኩታ ለባሽ” ተጋባዥ በመገረም ዝም ብሎ ይመለከት ነበር እንጂ ከእነርሱ አንድቸውን እንኳ ጠርቶ ለአጋፋሪዎቹ እንዲነግሩለት አልሞከረም ይህን ለማድረግ ቀድሞውንም አሳብ አልነበረውምና !

በዚህ ሁኔታ መቆየቱ ሌላ የባሰ ችግርን መጋበዝ እንጂ ሌላ ምንም የሚጠቅም ነገርን የማያስገኝ መሆኑን ሲያረጋግጥ የግብዣው ሰዓት በጣም እንዳያልፍበት ለተሽከርካሪ ነጂው (chauffeur) ተገቢውን መመሪያ ሰጥቶ በፍጥነት ወደቤቱ ኼደ እንደሥራ ጓደኞቹ ላታሙንና ጥቁቱን የፈረንጆቹን የክብር ልብስ ለብሶና በዚያ አጊጦ ወደቤተ መንግሥቱ ቀልጥፎ ተመለሰ፤ እዚያም ሲደርስ በዚያ በሚያውቀውና ሲመለከት በቆየው አቀባበል ገና ከሩቅ መንገዱ እየተከፈተለት ማንነቱም ሳይጠየቅ በግራና በቀኝ እየተሰገደለት ሰተት ብሎ ከግብሩ አዳራሽ ሲደርስ የእልፍኝ አስከልካዮች እጅ ነሥተውና በትሕትና ተቀብለው ስሙ ወደተጻፈበት ወንበሩ መርተው አስቀመጡት።

የግብሩ ሰዓት ደርሶ አጼው በዙፋናቸው ላይ እንደተቀመጡ ግብዣው ሲጀምር ያ ወደ ግብሩ እንዲገባ ተፈቀዶለት በክብር የተቀመጠው የኋለኛው ፈረንጅ የሚቀርብለትን ምግብና መጠጥ እያነሳ ለሰውነቱ ማጕረስና ማስጐንጨት ሳይኾን ለዚያ ለልብሱ ብቻ ይመግብና ያጠጣ ጀመር።

እዚያም በአጠገቡና በአካባቢው የተቀመጡት ተጋባዦች ወዲያ ወዲህ የሚራወጡት አሳላፊዎችም በድርጊቱ ተደንቀው እየተሣሣቁ ሣሉ ድርጊቱን ከሩቅ በመገረም ይመለከቱ የነበሩት አጼ፥ ያ፥ የሚች ባለሟላቸው ልጅ ለምን እንደዚያ እንዳደረገ በእልፍኝ አስከልካያቸው አማካይነት ቢያስጠይቁት “የተጋበዝኩበት አማካይነት ቢያስጠይቁት

“የተጋበዝኩት እኔ ሳልኾን ወይም ኢትዮጵያዊው ሰውነቴ ሳይኾን ይህ የተሸከምኩበት የፈረንጅ ልብሴ ስለኾነ ነው ! ” ብሎ መልሱን ሰጠ።

ከዚያ አያይዞም፣ ቀደም ሲል፣ እንደብርሃን ፀዳል በነጣው ኢትዮጵያዊ ልብሱ ተሸልሞ በመጣ ጊዜ በዚያ ልብሱ ምክንያት ብቻ በገዛ አገሩና በገዛ ቤተ መንግሥቱ አደባባይ በገዛ ወገኖቹ የደረሰበትን ውርደትና እንግልት በኋላ ደግሞ እንደጨለማ ድቅድቅ በጠቆረው የፈረንጅ ልብስ ተሸንቅጦ በተመለሰ ጊዜ የተበረከተለት አክብሮትና እንክብካቤ እንዴት እንደነበረ ኹሉንም አስረዳ።

ያ ድርጊት የዚያን ጊዜዪቱ ኢትዮጵያ፣ ሕዝቧን ይዛ በምን ኹኔታ ላይ እንዳለችና ወደየትስ አቅጣጫ እያመራች እንደኾነ ዛሬ የተደረሰባትን የውድቀት ፍጻሜ በአጠቃላይ የሚያመለክት፣ ከጀግና አርበኛ የተሰጠ ብርቱ የማስጠንቀቂያ ምልክት እንደነበረ ግልጽ ነው።

ይህን የመሰለውን ጀብድ የፈጸሙት የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ልጅ፣ ቆራጡ ኢትዮጵያዊ ብላታ ሢራክ እንደኾኑ ይነገራል።

ኢትዮጵያ ሆይ፥ ሀገራችን ! ረስቼስ እንደኾነ፣ ቀኜ ትርሳኝ፣
ያላሰብሁሽ እንደኾን፣ መላሴ ትናጋዬን ሰልቶ ይውጋኝ።

አቤቱ ፈጣሪያችን፣ በኢትዮጵያ ቀን፣ ጠላቶቿን ኹሉ አስብ፤
አፍርሷት፣ ኢትዮጵያን፣ እስከመሰረቷ ድረስ፣ የሚሉትንም ሕዝብ።

እናንት ትምክህተኞች፣ የኢትዮጵያ ጸሮች፥ የተነኰላችሁን ብድራት፤
የሚመልስ ነው አምላካችን፣ በፍትሕ በተአምራት፤
በሚጠሉሽ ላይ፣ በእውነት፥
በቅን ለሚፈርደው ንጉሥ፣ ምስጋናችን ይብዛለት።
ኢትዮጵያ ሆይ፥ ሀገራችን ! ረስቸሽ እንደኾነ ቀኜ ትርሳኝ።

* * * * * * *